# የ ECONOMIC DISPLACEMENT RELOCATION ASSISTANCE ማስታወቂያ:- ለፋይናንስ እርዳታ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ

የ Economic Displacement Relocation Assistance (EDRA፣ የምጣኔ ሃብታዊ መፈናቀል ዝውውር እርዳታ) ፕሮግራም 10% ወይም ተጨማሪ የቤት ኪራይ ጭማሪ ያገኙ ለገቢ ብቁ ተከራዮች ለማዘዋወር የገንዘብ እርዳታ ለማግኘት እንዲያመለክቱ እድል ይሰጣል። **እባክዎ የመልቀቅ እቅድ ካልዎት ብቻ ያመልክቱ።**

## ጥቅማ ጥቅሙ ምንድነው እና ማነው የሚያቀርበው?

በሲያትል ከተማ አከራዮች የቤት ወጪዎን ቢያንስ 10% ሲጨምሩ ስለዚህ ፕሮግራም ለተከራዮች እንዲያሳውቁ ያስፈልጋል። የ Seattle Department of Construction and Inspections (SDCI፣ የሲያትል የግንባታ እና ፍተሻ ክፍል) ከባለንብረቱ ገንዘብ ይሰበስባል እና ገንዘቡን ብቁ ለሆኑ ቤተሰቦች ያከፋፍላል። ከተፈቀደ፣ ተከራዮች **ከወርሃዊ የቤት ወጪ እስከ 3 እጥፍ የሚደርስ ነጠላ ክፍያ ከከተማው ይደርሳቸዋል።**

## ብቁ መሆኔን እንዴት አውቃለሁ?

በዚህ ተጠቃሚነት ብቁ ለመሆን፣ ማሟላት ያለብዎት የሚከተሉትን ነው:-

1. በ 7/1/2022 ወይም ከዚያ በኋላ **አጠቃላይ የመኖሪያ ቤት ወጪዎችን ቢያንስ በ 10% እንደሚጨምር የሚያሳይ** ማሳወቂያ ከተቀበሉ። ይህ በ 12 ወራት ውስጥ የአንድ ጭማሪ ወይም ብዙ ጭማሪ ማሳወቂያ ሊሆን ይችላል።
2. ጠቅላላ የቤተሰብ **ገቢ ከ Area Median Income (AMI፣ የአካባቢው መካከለኛ ገቢ) በ 80% ወይም በታች ካልዎት።**

| የቤተሰብ መጠን | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 80% AMI **(2022)** | $66.750 | $76.250 | $85.800 | $95.300 | $102.950 | $110.550 | $118.200 | $125.800 |

3. ለመልቀቅ ያስቡ እና ለአከራይዎ የመልቀቂያ ቀን ለማቅረብ ዝግጁ ይሁኑ።

## የማመልከት ሂደት እና የጊዜ ሰሌዳ ምንድነው?

1. **ተከራዮች ለአከራያቸው እንደሚለቁ በጽሁፍ በማሳወቅ አለባቸው።** በአጠቃላይ፣ የሚለቀቅበት ቀን የኪራይ ውሉ የሚያልቅበት ወይም የተከራየው ከወር እስከ ወር ከሆነ ወርሃዊ የኪራይ ጊዜ የሚያበቃበት መሆን አለበት። **ማመልከት ለክፍያ ብቁነት ዋስትና አይሰጥም።**
2. ተከራዮች የተከራይ ጭማሪ ማስታወቂያ ከተቀበሉ በኋላ በማንኛውም ጊዜ (ጭማሪው ተግባራዊ ከሆነ እስከ 60 ቀናት ድረስ) ማመልከት ይችላሉ። በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ ማመልከት ካልቻሉ፣ በማመልከቻው የመጨረሻ ቀን *በፊት* ባሉ አማራጮች ላይ **ለመወያየት እባክዎን ወደ 206-684-5700 ይደውሉ።**
3. SDCI ማመልከቻዎች የመለከት እና **ያለቀ ማመልከቻዎን መቀበሉን በ 10 ቀናት** ውስጥ ያሳውቃታል። ከጸደቀ፣ SDCI **በ 14 ቀናት ውስጥ ቼክ ያወጣል፣** እና **በማመልከቻዎ ውስጥ እንዳስገቡት የመልቀቂያ ቀን ድረስ መልቀቅ ይኖርቦታል።**

## እንዴት የበለጠ ማወቅ እና ማመልከት እችላለሁ?

ስለ EDRA ፕሮግራም የበለጠ ይወቁ፣ በቀጥታ መስመር ያመልክቱ ወይም ከድህረገጻችን:- www.seattle.gov/rentinginseattle/edra የወረቀት ማመልከቻ ያግኙ።

**አሁንም ጥያቄዎች ካልዎት ወይም እርዳታ ይፈልጋሉ?** በሲያትል የ SDCI የ Renting in Seattle (ኪራይ በሲያትል) የእርዳታ መስመር ላይ በ 206-684-5700 ይደውሉ። የቋንቋ እርዳታ ይገኛል

206-684-5700 ይደውሉ ወይም www.seattle.gov/rentinginseattle/edra።